# አርሲ ዩኒቨርሲቲ

# የአስር ዓመት ስትራቴጂያዊ ዕቅድ

## (2013-2022 ዓ.ም)

# መግቢያ

የአርሲ ዩኒቨርሲቲ በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን መባቻ ከተቋቋሙት አስራ አንድ ዩኒቨርሲቲዎች ውስጥ አንዱ ሲሆን፤ ዩኒቨርሲቲው በ2006 ዓ.ም. በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 803/2005 ተቋቁሞ ከ2007 ዓ.ም መጀመሪያ ጀምሮ ተማሪዎችን ተቀብሎ በማስተማር፣ ጥናትና ምርምር እንዲሁም የማህበረሰብ አገልግሎቶች ለአካባቢው ማህበረሰብ ተደራሽ በማድረግ ላይ ይገኛል።

የአርሲ ዩኒቨርሲቲ አምስት ኮሌጆችንና አንድ የህግ ት/ቤት በአሰላና በበቆጂ ካምፓሶች በቅድመ ምረቃ መደበኛ 41፣ ኤክስቴንሽን 11፣ በክረምት 9 እንዲሁም በድህረ ምረቃ በመደበኛ 18፣ በኤክስቴንሽን 13 እና በክረምት 8 በ41 የትምህርት ክፍሎች በመሰጠት ላይ ይገኛል። የተማሪ ቅበላ አቅም በመደበኛ፣ በተከታታይና በPGDT ፕሮግራም ወንድ 6677 ሴት 3236 በአጠቃላይ 9913 ተማሪዎችን ተቀብሎ በ2012 በማስተማር ላይ ይገኛል። ከ2009 ዓ.ም. ጀምሮ በተለያዩ የትምህርት ፕሮግራሞች በቅድመ ምረቃ 4097 ወንድ 2262 ሴት በድህረ ምረቃ 1341 ወንድ 153 ሴት በአጠቃላይ 7853 ተማሪዎችን አስመርቋል። እንዲሁም በPGDT 1603 ወንድ 807 ሴት HDP ወንድ 78 ሴት 20 በአጠቃላይ በድምሩ 2508 ተማሪዎችን አስመርቋል።

የዩኒቨርሲቲውን የሰው ኃይል በተመለከተ መምህር 865 (ወንድ 679 ሴት 186)፤ የአካዳሚክ ረዳት ቴክኒክ ሰራተኛ 48 (ወንድ 38 ሴት 10 )፣ የጤና ባለሞያዎች 350 (ወንድ 181 ሴት 169) ሲሆኑ የአስተዳዳር ሠራተኞች ቁጥር 1946 (ወንድ 979 ሴት 967) አጠቃላይ የተቋሙ ሠራተኞች 3204 (ወንድ 1869 ሴት 1335) ሠራተኞች አሉት። በስራ ላይ ያሉ መምህራን የትምህርት ደረጃ ስንመለከት በሦስተኛ ዲግሪ 81 (ወንድ 80 ሴት 1) በሁለተኛ ዲግሪ 408 (ወንድ 334 ሴት 74) በመጀመሪያ ዲግሪ 78 (ወንድ 54 ሴት 24) አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛሉ። በተጨማሪ በትምርት ላይ ያሉ መምህራን 298 ሲሆኑ በሁለተኛ ዲግሪ 114 (ወንድ 84 ሴት 30) እና በሦስተኛ ዲግሪ 184 (ወንድ 127 ሴት 57) ናቸው።

የተቋሙን የአስር አመት ስትራቴጂ ዕቅድ በ4ቱ የልህቀት ማዕከሎች "Center of excellence" (በግብርና፣ በጤና ፣ቴክኖሎጂና ኢንጂነሪንግ) ታሳቢ በማድረግ፣ በአራት (4) የትኩረት መስኮች፣ ስምንት (8) ግቦችን በማካተት ተዘጋጅቷል።

# የአርሲ ዩኒቨርሲቲ አመሰራረትና እድገት

ዩኒቨርሲቲው የተቋቋመበት አከባቢ አርሲ ዞን በኢትዮጵያ ውስጥ የግብርና ኤክስቴንሽን የተጀመረበት አካባቢ በመሆኑ እምቅ በሆነ የስንዴ ምርት እና ወተት ምርት ይታወቃል፡፡ ዞኑ በአገር አቀፍ ደረጃ አረንጓዴና ተስማሚ የአየር ሁኔታ ያለው ነው፡፡ እንዲሁም በዓለም ደረጃ ኮከብ ለሆኑት የኢትዮጵያ አትሌቶች እናት መሬት በመባልም ይታወቃል፡፡

አካባቢው የChilalo Agricultural Development Unit (CADU) በ1967እ.ኤ.አ በስዊድን መንግስት የተቋቋመ ሲሆን በመቀጠል CADU ወደ ARDU በ1975 እ.ኤ.አ የተቀየረ በመሆኑ በዚህ ጊዜ የአርሲ የገጠር ልማት ክፍል (ARDU) ፕሮጀክቱን ወደ ሁለት ተጨማሪ የአርሲ አውራጃዎች (ጢቾ እና አርባ-ጉጉ) አስፋፋ፡፡ እንዲሁም  በእ.ኤ.አ. 1985 SEAD (የደቡብ ምስራቅ እርሻ ልማት ዞን) አርሲን እና የባሌ ክልልን በከፊል በማጠቃለል 2.7 ሚሊዮን ነዋሪዎችን የምርጥ ዘርና የማደበሪያ ተቃሚ አድርጓል፡፡ በእ.ኤ.አ. 2001 የግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና (ATVET) በመባል የተቋቋመ ሲሆን የግብርና ሙያተኞችን በማሰልጠን የግብርና እክስቴንሽን እንዲያድግ አሰተዋጽኦ አድረጓል፡፡ በ2008 እ.ኤ.አ በአዳማ ዩኒቨርሲቲ የግብርና ትምህርት ቤት በመሆን በመጀመሪያ ዲግሪ በአምስት የትምህር መስኮች ሲያስተምር ቆይቷል፡፡

የአርሲ ዩኒቨርሲቲ በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን መባቻ ከተቋቋሙት አስራ አንድ ዩኒቨርሲቲዎች ውስጥ አንዱ ሲሆን፤ ዩኒቨርሲቲው በ2006 ዓ.ም. በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር **803/2005** ተቋቁሞ ከ2007 ዓ.ም መጀመሪያ ጀምሮ የCADU, ARDU, SEAD, ATVET እና የASTU የነበሩትን መሠረተ ልማቶችና በሥሩ የሚገኙ 400 ሄክታር መሬት፣ የአሰላ አጠቃላይ ሆስፒታልና የበቆጂ ATVET ካምፓስ በማጠቃለል በ5 ኮሌጆችና በአንድ ትምህርት ቤት ተማሪዎችን ተቀብሎ በማስተማር፣ ጥናትና ምርምር እንዲሁም የማህበረሰብ አገልግሎቶች ለአካባቢው ማህበረሰብ ተደራሽ በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡

**(ከድንገተኛ ክስታቶች የተገኘ ልምድ)**

- ***ታሳቢ ስጋቶችና የመፍትሔ እርምጃዎች*** (Cross cutting Issues, lessons Learnt and Measures to be taken)

***ታሳቢ ስጋቶች***

- ከኮቪድ 19 ጋር ተያይዞ የማማር ማስታማሩ ሀደት ማስተጓጎሉ
- በፖለቲካዊ አለመረጋጋት እና በኮቪዴ 19 ወረርሽኝ ምክንያት ተማሪዎች ወደ ተቋሙ ተመልሰው ለመማር ስጋት መፈጠሩ
- ከኮቪድ 19 ጋር ተያይዞ በየደረጃው የሚያስፈልጉ የመመርመሪያ ማሽነሪዎችና ግብዓቶች በጊዜ አለመሟላታቸው
- ከኮቪድ 19 ጋር ተያይዞ በአጠቃላይ በሠራተኞች ዉስጥ ስጋት መፈጠሩ
- የበረሃ አምበጣ በሀገርቷ በመከሰቱ ለዩኒ,ቨርሲቲውና ለአከባቢው ማህብረስብ ስጋት መሆኑ
- የበረሃ አምበጣና ለመሰል ችግሮች መቆጣጠሪያ የሚሆንና ለመመራመር የሚያስችል ቅድመ-ዝግጂት አለማኖሩ

***የተገኘ ተሞኪሮ***

- Virtual communication and operation(Zooming, Webinar and Teams)
- Work at distance
- On line learning and teaching
- Hygienes and sanitization (Personal, community, environmental and institutional)
- Safety
- Open window service
- Reduced physical contact
- Enhanced digital communication among stakeholders
- Group /team work to reduce risks and impacts (desert  locust)
- Use of endogenous knowledge to reduce natural hazards like desert locust

የውስጣዊና ውጫዊ የአካባቢ ዳሰሳ መሠረት በማድረግ ዩኒቨርሲቲያችን ቀጥሎ የተዘረዘሩትን ትኩረት የሚሹ ጉዳዬችን (Strategic Issues) በመለየት ተቋሙ ትኩረት ሰጥቶ መስራት ያለባቸው ጉዳዮችን እንደሚከተለው አስቀምጦል-

1. የትምህርት ጥራትና አግባብነትን በማስጠበቅ ብቁና ተወዳዳሪ ባለሙያዎችን ማፍራት፣
2. የተግባር ትምህርት መስጫ ቦታዎችን መገንባትና ማደራጀት (ቤተ-ሙከራዎች፣ቤተ-መጽሃፍት፣የኢ.ኮ.ቴ መሠረተ ልማት፣ ዎረክሾፖች፣ኢንዱስትሪዎች…)
3. ከአለም አቀፋዊና ሀገራዊ ተቋማት ጋር አብሮ የማስራት ትስስር (Partnership) ማፍጠር
4. ከኢንዱስትሪዎችና ከተለያዩ ተቋማት ጋር በመተባባር የሙያተኛ ልውውጥ (Staff exchange) ማድረግ
5. የተቋሙን ተቀባይነት በማሳደግ አለም አቀፋዊ ተወዳዳሪነትን ማረጋገጥ፣
6. የቴክሎኖጂና የፈጠራ ኃሳቦችን በማፍለቅ የማህበረሰብ ተጠቃሚነትን ማሻሻል፣
7. ትምህርት ለሁሉም ዜጋ በእኩልነት እንዲዳረስ በማድረግ ፍትሃዊነትን ማረጋገጥ
8. የተቋሙን የኢኮኖሚ አቅም በመገንባትና የሐብት ብክነትን በመቀነስ አጠቃቀምን ማሳደግ፣
9. የተማሪዎችንና የኢንዱስትሪዎችን በምርምርና በማህበረሰብ አገልግሎት ያላቸውን ተሳትፎ ማሳደግ፣
10. ሁሉን አቀፍ የጤና አገልግሎት በማስፋፋትና Smart health Care ስርዓትን በመዘርጋት የማህበረሰቡን ተጠቃሚነት ማሳደግ
11. የዩኒቨርሲቲ ዋና ዋና የትኩረት መስክ ያልሆኑ አገልግሎቶችን “out source” በማድረግ የተቋሙን ውጤታማነት ማሳደግ፣
12. የዩኒቨርሲቲውን የሰው ሐብት አቅም መገንባት፣

## ተልዕኮ

አርሲ ዩኒቨርሲቲ ተግባር ተኮር የሆነ የመማር ማስተማር ዘዴን በመጠቀም፣ችግር ፈቺ ምርምሮችን በማካሄድ፣ ከኢንዱስትሪዎች ጋር የተቀናጀ የማህበረሰብ አገልግሎቶችን በመስጠት፣ ብቃት ያላቸውና በስነ-ምግባር የታነፁ ምሩቃንን በማፍራት ቀጣይነት ላለው የሀገሪቱ ዕድገት አስተዋፅኦ ለማበርከት ይተጋል::

## ራዕይ

በ2022 ዓ.ም. በምስራቅ አፍሪካ ተዋቂና ተመራጭ የአፒላይድ ሳይንስ ዩኒቨርሲቲ ሆኖ መገኘት ነው::

## መሪ ቃል

እንደ ከዋክብት አትሌቶቻችን፣ የላቁ ባለሞያዎችን!

## እሴቶች

እሴቶች አንድ ተቋም የሚመራባቸው መሰረታዊ እምነቶች ናቸው:: በዚህ መሰረት አርሲ ዩኒቨርሲቲ ዘጠኝ እሴቶችን አስቀምጧል ::

## የእሴቶች

1. ብዝሀነትን ማክበር
2. ተግባር ተኮር
3. ጥራት ተኮር
4. በጋራ መስራት
5. አለም አቀፋዊነት
6. አካባቢያዊ ጥበቃ
7. ፈጠራ
8. ሙያዊ ስነምግባር

## የተቋሙ የትኩረት መስኮች

I. ተግባር ተኮር የመማር ማስተማር (Practice based teaching and learning)
II. ችግር ፈቺ የጥናትና ምርምር (Applied/action based Research)
III. ማህበረሰብ ተኮር አግልግሎትና አሳታፍ የኢንደስቲሪ ትስስር (community oriented and industry engaged services)
IV. ሁለንተናዊ የጤና አገልግሎት (Comprehenssive Health Care)

## የተቋሙ ግቦችና ለግቡ የተሰጠ ክብደት

| ስትራቴጂያዊ ግቦች | የግብ ክብደት |
|---|---|
| ግብ 1. የደንበኞችን/የተገልጋዮችን ተሳትፎና እርካታ ማሳደግ | 15 |
| ግብ 2. የዩኒቨርሲቲ ኢንዱስቲሪ ትስስርና አጋርነትን በማሻሻልና በማስፋፋት ችግር ፋቺ የጥናትና ምርምር ዉጤቶችን ተደራሽነት ማሳደግ | 12 |
| ግብ 3. የትምህርት ጥራት፣አግባብነት፣ተደራሽነትና ፍትዊነትን ማሳደግ | 25 |
| ግብ 4. የሳይንስ ባህል ግንባታ፣ የቴክኖሎጂና የፈጠራ ሥራዎችን በማሸጋጋር የማህበረሰብ አገልግሎትን ማጠናከር | 10 |
| ግብ 5. የማህበረሰብና የህክምና አገልግሎት ዘርፎች ማስፋፋት | 12 |
| ግብ 6. የተቋሙን የአፈፃፀም ክትትልና ግምገማ ስርዓት ማጠናከር | 6 |
| ግብ 7. የተቋሙን አቅምና ብቃት ማሳደግ | 10 |
| ግብ 8. የተቋሙን መሠረተ ልማቶችና ፋሲሊቲዎችን ማሳደግ | 10 |

የ10 አመት የልማት እቅድ በውስጡ ስምንት ግቦችንና ሰላሳ አምስት ስትራቴጂክ ኢላማ ተቀርጾለት የተቋሙ ልማታዊ እቅድ ተዘጋጅቷል፡፡

## የአርሲ ዩኒቨርሲቲ ለ2013-2022 በጀት ዓመት የግቦች ማስፈፀሚያ በጀት ትንበያ

| ስትራቴጂያዊ ግቦች | 2013 | 2014 | 2015 | 2016 | 2017 | 2018 | 2019 | 2020 | 2021 | 2022 | ጠ/ድምር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ግብ 1. የደንበኞችን/የተገልጋዮችን ተሳትፎና እርካታ ማሳደግ | 144,996,132.64 | 156,355,804.75 | 168,722,850.74 | 184,926,543.08 | 202,533,311.70 | 217,564,561.70 | 232,595,811.70 | 247,627,061.70 | 262,658,311.70 | 277,689,561.70 | **2,095,669,951.40** |
| ግብ 2. የዩኒቨርሲቲ ኢንዱስቲሪ ትስስርና አጋርነትን በማሻሻልና በማስፋፋት ችግር ፋቺ የጥናትና ምርምር ዉጤቶችን ተደራሽነት ማሳደግ | 23,583,877.37 | 25,471,617.24 | 28,562,616.93 | 31,380,673.33 | 34,468,118.62 | 37,655,618.62 | 40,843,118.62 | 44,030,618.62 | 47,218,118.62 | 50,405,618.62 | **363,619,996.59** |
| ግብ 3. የትምህርት ጥራት፣ አግባብነት፣ተደራሽነትና ፍትዊነትን ማሳደግ | 152,956,331.76 | 165,400,644.06 | 180,639,261.22 | 197,792,627.71 | 216,365,398.43 | 231,490,398.43 | 246,615,398.43 | 261,740,398.43 | 276,865,398.43 | 291,990,398.43 | **2,221,856,255.31** |
| ግብ 4. የሳይንስ ባህል ግንባታ፣ የቴክኖሎጂና የፈጠራ ሥራዎችን በማሸጋጋር የማህበረሰብ አገልግሎትን ማጠናከር | 21,672,684.08 | 23,407,243.00 | 26,244,894.93 | 28,834,362.90 | 31,671,395.65 | 34,618,270.65 | 37,565,145.65 | 40,512,020.65 | 43,458,895.65 | 46,405,770.65 | 334,390,683.81 |
| ግብ 5. የማህበረሰብና የህክምና አገልግሎት ዘርፎች ማስፋፋት | 113,545,785.60 | 121,959,066.47 | 127,941,551.73 | 140,286,794.63 | 153,720,665.25 | 164,961,290.25 | 176,201,915.25 | 187,442,540.25 | 198,683,165.25 | 209,923,790.25 | **1,594,666,564.93** |
| ግብ 6. የተቋሙን የአፈፃፀም ክትትልና ግምገማ ስርዓት ማጠናከር | 1,116,345.92 | 1,198,946.92 | 1,256,238.30 | 1,377,404.84 | 1,509,239.42 | 1,619,239.42 | 1,729,239.42 | 1,839,239.42 | 1,949,239.42 | 2,059,239.42 | **15,654,372.52** |
| ግብ 7. የተቋሙን አቅምና ብቃት ማሳደግ | 122,113,373.19 | 131,629,896.56 | 141,523,989.11 | 155,107,765.82 | 169,865,117.73 | 182,348,867.73 | 194,832,617.73 | 207,316,367.73 | 219,800,117.73 | 232,283,867.73 | **1,756,821,981.05** |
| ግብ 8. የተቋሙን መሠረተ ልማቶችና ፋሲሊቲዎችን ማሳደግ | 600,000,000.00 | 650,000,000.00 | 780,000,000.00 | 858,000,000.00 | 943,800,000.00 | 1,043,800,000.00 | 1,143,800,000.00 | 1,243,800,000.00 | 1,343,800,000.00 | 1,443,800,000.00 | **10,050,800,000.00** |
| **ጠቅላላ ድምር** | **1,179,984,530.55** | **1,275,423,219.00** | **1,454,891,402.96** | **1,597,706,172.30** | **1,753,933,246.80** | **1,914,058,246.80** | **2,074,183,246.80** | **2,234,308,246.80** | **2,394,433,246.80** | **2,554,558,246.80** | **18,433,479,805.61** |

**ምንጭ፡-** ከመንግስትና ከውስጥ ገቢ

(በሚሊየን ብር)

# የአርሲ ዩኒቨርሲቲ ከ2013-2022 በጀት ዓመት የፕሮግራም በጀት ትንበያ

| የበጀት ባለቤት | የፕሮግራም ስም | የወጪ በጀት ዓይነት | ዓመታዊ የወጪ በጀት ትንበያ | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | 2013 | 2014 | 2015 | 2016 | 2017 | 2018 | 2019 | 2020 | 2021 | 2022 | ጠ/ድምር |
| አርሲ ዩኒቨርሲቲ | ሥራ አመራር | የመደበኛ ወጪ ድምር | 203,961,234.46 | 218,961,234.46 | 228,961,234.46 | 251,857,357.90 | 277,043,093.71 | 297,043,093.71 | 317,043,093.71 | 337,043,093.71 | 357,043,093.71 | 377,043,093.71 | 2,865,999,623.54 |
| | | የውስጥ ገቢ | 19,307,950.16 | 20,828,150.00 | 22,286,425.00 | 23,623,610.50 | 24,804,790.85 | 26,804,790.85 | 28,804,790.85 | 30,804,790.85 | 32,804,790.85 | 34,804,790.85 | 264,874,880.76 |
| | | **ድምር** | **223,269,184.62** | **239,789,384.46** | **251,247,659.46** | **275,480,968.40** | **301,847,884.56** | **323,847,884.56** | **345,847,884.56** | **367,847,884.56** | **389,847,884.56** | **411,847,884.56** | **3,130,874,504.30** |
| | መማር ማስተማር | ከመንግስት ግምጃ ቤት | 242,309,371.54 | 262,047,593.75 | 287,045,945.40 | 315,750,539.98 | 347,325,593.35 | 372,325,593.35 | 397,325,593.35 | 422,325,593.35 | 447,325,593.35 | 472,325,593.35 | 3,566,107,010.77 |
| | | የውስጥ ገቢ | 35,793,049.84 | 38,680,850.00 | 41,389,075.00 | 43,872,419.50 | 46,066,040.15 | 48,566,040.15 | 51,066,040.15 | 53,566,040.15 | 56,066,040.15 | 58,566,040.15 | 473,631,635.24 |
| | | **ድምር** | **278,102,421.38** | **300,728,443.75** | **328,435,020.40** | **359,622,959.48** | **393,391,633.50** | **420,891,633.50** | **448,391,633.50** | **475,891,633.50** | **503,391,633.50** | **530,891,633.50** | **4,039,738,646.01** |
| | ጥናትና ምርምር | ከመንግስት ግምጃ ቤት | 40,389,058.78 | 43,617,906.00 | 48,854,283.02 | 53,676,035.83 | 58,959,269.35 | 64,771,769.35 | 70,584,269.35 | 76,396,769.35 | 82,209,269.35 | 88,021,769.35 | 627,480,399.72 |
| | የማህበረሰብ አገልግሎት | ከመንግስት ግምጃ ቤት | 38,223,865.78 | 41,287,484.79 | 46,354,440.08 | 50,926,208.59 | 55,934,459.39 | 60,746,959.39 | 65,559,459.39 | 70,371,959.39 | 75,184,459.39 | 79,996,959.39 | 584,586,255.57 |
| | መደበኛና የውስጥ ገቢ ድምር | | **579,984,530.55** | **625,423,219.00** | **674,891,402.96** | **739,706,172.30** | **810,133,246.80** | **870,258,246.80** | **930,383,246.80** | **990,508,246.80** | **1,050,633,246.80** | **1,110,758,246.80** | **8,382,679,805.61** |
| | ካፒታል በጀት | ከመንግስት ግምጃ ቤት | 600,000,000.00 | 650,000,000.00 | 780,000,000.00 | 858,000,000.00 | 943,800,000.00 | 1,043,800,000.00 | 1,143,800,000.00 | 1,243,800,000.00 | 1,343,800,000.00 | 1,443,800,000.00 | 10,050,800,000.00 |
| **ጠቅላላ ድምር (መደበኛና ካፒታል)** | | | **1,179,984,530.55** | **1,275,423,219.00** | **1,454,891,402.96** | **1,597,706,172.30** | **1,753,933,246.80** | **1,914,058,246.80** | **2,074,183,246.80** | **2,234,308,246.80** | **2,394,433,246.80** | **2,554,558,246.80** | **18,433,479,805.61** |